# ከመጋቢት 27/2014 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30/2014 ዓ.ም የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

የሚኒስትሮች ም/ቤት መስከረም 23 ቀን 2001 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የነዳጅ ምርቶች ዋጋ በየወሩ እንዲከለስ በሰጠው መመሪያ መሠረት ከመጋቢት 27/2014 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30/2014 ዓ.ም ድረስ ተግባራዊ የሚሆነው የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን አስመልክቶ ይህ መግለጫ ተዘጋጅቷል፡፡

ነባራዊ የዓለም የነዳጅ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ በየወሩ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት የሀገራችን የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በወቅታዊ የዓለም ነዳጅ ዋጋ መሠረት ተሰልቶ በሚመጣው ተግባራዊ ቢደረግ አሁን በተግባር እንዲሸጥበት ከተወሰነው የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ የተለየ ይዘት ይኖረው ነበር፡፡

ነገር ግን መንግስት የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በተረጋጋ ሁኔታ እንዲቀጥል ለማስቻል በሚያዚያ ወር/2014 ዓ.ም የቤንዚን እና የናፍጣ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በመጋቢት ወር/2014 ዓ.ም ሲሸጥበት በነበረው ያለምንም ለውጥ በነበረበት እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡

ነገር ግን የአውሮፕላን ነዳጅ፣ የከባድ ጥቁር ናፍጣ እና ቀላል ጥቁር ናፍጣ የመሸጫ ዋጋ በዓለም አቀፍ ዋጋ መሰረት ተሰልቶ የመጣው ወደ ተጠቃሚው እንዲተላለፍ የተወሰነ መሆኑን እያሳወቅን የወቅታዊ የዓለም አቀፍ የነዳጅ ምርቶች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሸማቹ ህብረተሰብ የነዳጅ ምርቶችን በቁጠባ የመጠቀም ባህሉን በማዳበር መንግስት ለዘርፉ የሚያወጣውን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ እንዲሁም ድጎማ ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪ እያቀረብን በዓለም ገበያ ላይ የሚኖረውን የነዳጅ ዋጋ መነሻ በማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ ማስተካከያ ሊደረግ የሚችል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

*መጋቢት 26 ቀን 2014 ዓ.ም*

*የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር*

እንዳለው መኮንን አለሚ
ሚኒስትር ዴኤታ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic Of Ethiopia
Ministry Of Trade & Regional Integration

ቀን/Date: 26 መጋቢት 2014
ቁጥር/No: 01.1.22.9/9591

**ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን**
**ለፋና ብሮድካስት ኮርፖሬሽን**
**ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት**
**ለዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል**
**ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት**
**አዲስ አበባ**

**ጉዳዩ፡- ከመጋቢት 27/2014 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30/2014 ዓ.ም የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን ይመለከታል፤**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 23 ቀን 2001 ዓ.ም. ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የነዳጅ ምርቶች ዋጋ በየወሩ እንዲከለስ ውሳኔ ማሳለፉ ይታወቃል፡፡

በዚህም መሰረት ከመጋቢት 27/2014 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30/2014 ዓ.ም የነዳጅ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ በተመለከተ የተዘጋጀ መግለጫ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration

ዳሰው መኮንን ለሲሜ
ሚኒስትር ዲኤታ

አባሪ- 1 ገጽ

እንዲያውቁት
- ለክቡር የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚንስትር
  **ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር**

ግልባጭ፡-
- ለነዳጅ እና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦትና ስርጭት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን
  አዲስ አበባ
- ለህዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት
- ለንግድ ዕቃዎች ዋጋ ጥናት፣ ክትትል እና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት
  **ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር**